# ምስጢረ ንስሐ

## <u>ጥያቄ፤</u>ንስሐ ማለት ምን ማለት ነው?

ንስሐ ማለት እግዚአብሔርንና ሰዉን በመበደል የእግዚአብሔርንና ትእዛዝ (ሕግ) በመተላለፍ ከፈጸሙት ኃጢአት መጸጸትና ማዘን «በድየለሁ አጥፍቻለሁ» ብሎ እግዚአብሔርን መለመንና ይቅርታን መጠየቅ ማለት ነው።

## <u>ጥያቄ፤</u>መናዘዝ ማለትስ ምን ማለት ነው?

መናዘዝ ማለትስ የሠሩትን ኃጢአትና የፈጸሙትን በደል በሙሉ በንስሐ አባት አማካኝነት ለእግዚአብሔር መንገር ማለት ነዉ። ለንስሐ አባት መንገር ማለት ለእግዚአብሔር መንገር ማለት ነዉና።«ኃጢአትየ ነገርኩ ወአበሳየ አኀባእኩ ወአቤ አስተዋዲ ርእስየ እግዚአብሔር በአንተ ኃጢአትየ»ኃጢአቴን ነገርሁ በደሌን አልደበቅሁም መተላለፌን ሁሉ ለእግዚአብሔር እናገራለዉ አልሁ ሲል ቅዱስ ዳዊት ተናግሮአል፤ ይኸዉም ንስሐ መግባትና የሠሩትን ኃጢአት በሙሉ ለእግዚአብሔር መናዘዝ (መንገር) የሚገባ መሆኑን ያረጋግጣል (መዝ ፴፩-(፴፪)-፭)።

## <u>ጥያቄ፤</u> ምስጢረ ንስሐ ማለት ምን ማለት ነወ?

ንስሐ በመግባትና በመናዘዝ በንስሐ አባት አማካኝነት መንፈስ ቅዱስ ንስሐ ለገቡና ለተናዘዙ ሥርየተኃጢአትን ስለሚሰጣቸውና ከኃጢአትና ከበደል ንጹሕ ስለሚያደርጋቸዉ የማንጻቱንም ሥራ የሚፈጽመዉ መንፈስ ቅዱስ በመሆኑ ንስሐ ምስጢር ይባላል። «መንፈስ ቅዱስ ባወቀው ኃጢአታችሁን ይቅር ይበላችሁ» እያሉ ካህናት «እግዚአብሔር ይፍታ» የሚሉት ስለዚህ ነው።

## <u>ጥያቄ፤</u> ንስሐ ስንት ክፍል አሉት?

፩ኛ/ ጥምቀተ ክርስትና ከመሰራትዋ በፊት የበደሉ ሰዎች በየጊዜዉ ወደ እግዚአብሔር እየተመለሱ ሲፈጽሙት የነበረውን የንስሐና የኑዛዜ ሥርዓት ነዉ። እንደዚሁም ዮሐንስ መጥምቅ ሲሰብከው የነበረው የንስሐ ጥምቀት ነው። ዮሐንስ መጥምቅ «መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ» ብሎ በይሁዳ ምድረ በዳ እየሰበከ መጣ። «የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውን አቅኑ...» እያለ ያን ጊዜም ኢየሩሳሌም ይሁዳም ሁሉ በዩርዳኖስ ዙሪያ ያለ አገር ሁሉ ወደ እርሱ ይመጡ ነበር። ኃጢአታቸውንም እየተናዘዙ በዩርዳኖስ ወንዝ ከእርሱ (ከዮሐንስ) ይጠመቁ ነበር (ማቴ ፫፡ ፩-፮ ማር ፩፡ ፩ ፰ ሉቃስ ፫፡፫-፲፯)።

፪ኛ/ ጥምቀተ ክርስትና ከተሠራች በኋላ እያንዳንዱ ክርስቲያን ከፈጸመው ኃጢአትና ከሠራው በደል በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ የሚፈጽመው የንስሐና የኑዛዜ ሥርዓት ነው።

ንስሐ ለማንውም ሰው እጅግ አስፈላጊ ነው። በቀድሞ ዘመነ እስራኤላውያን በየጊዜው ሕገ እግዚአብሔርን በመተላለፍ ኃጢአት ይፈጽሙ ነበር። እግዚአብሔር ግን በየጊዜው ነቢያትን እየላከ እስራኤላውያን ኃጢአት መሥራታቸውን ትተው በንስሐ ወደ ፈጣሪያቸው እንዲመለሱ በነቢያት አንደበት ይመክራቸው ነበር።

ለምሳሌ በነቢዩ በኢሳይያስ አንደበት እግዚአብሔር ያስተላለፈው የንስሐ ጥሪ እንዲህ የሚል ነው፤«ንዑ ንትዋቀስ ይቤ እግዚአብሔር እመኒ ኮነ ኃጢአትክሙ ከመ ኳኳ አነ አጻዐድዎ ከመ በረድ ወእመኒ ቄሐ ከመ ለይ አነ አነጽሖ ከመ ጸምር» «ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች እንደ ደም ብትቀላም እንደ ባዘቶ ትጠራለች (ኢሳ ፩፤ ፲፰)።

በሌላ ጊዜም እግዚአብሔር የበደሉትን በንስሐ ወደ ምሕረቱ ሲጠራ በነቢዩ አንደበት እንዲህ ብሎአል «አነኬ ውእቱ ዘእደመስሶን ለኃጣውኢከ ወኢይዜከሮን እንከ ለአበሳከ ነዓ ንትዋቀስ ወንግርአንተ ለኃጣውኢከ ቅድመ ከመ ትጽደቅ»፣ «መተላለፍህን እምደመስስልህ ኀጢአትህ ንም ይቅር እምልህ እኔ ነኝ ስለዚህ ና እንዋቀስ ትጸድቅህም ዘንድአስቀድመህ ኀጢአትህን ተ ናዘዝ» (ኢሳ.፵፫-፳፭-፳፮)

ዮሐንስ መጥምቅ እንዳደለገው ሁሉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላካዊ ሥራውን የጀመረዉ ሰውን ሁሉ በንስሐ ወደ እግዚአብሔር በመንግሥቱ በመጥራት ነው (ማቴ ፬-፲፯ ማር ፩-፲፭) ይልቁንም ራሱ ጌታችን በኃጢአት ደዌ የተያዙትን ሰዎች በሙሉ ወደንስሐ ለመጥራት የመ ጣ መሆኑን ሲያረጋግጥ «ኃጢአተኞችን ወደ ንስሐ ለመጥራት እንጅ ጻድቃንን ልጠራ አልመ ጣሁም»ሲል አስተምሮአል (ማቴ ፱-፲፫)።

ንስሐና ኑዛዜ እያንዳንዱ ሰው በብቸኝነት ስለ ራሱ ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት ዝቅ ብሎና ተዋርዶ የሚፈጽመው መንፈሳዊ ምስጢር ነው። ለምሳሌ ነቢዩ ዳዊት ለፈጸመው ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት ንስሐ ገብቶና ተናዝዞ እግዚአብሔር ስለስመነ ይቅርታ (ሥርየትን) አግኝ ቶአል (መዝ-፶) ሕዝቅያስም ከኃጢአቱና ከደዌው ይፈወስ ዘንድ እያለቀሰ ንስሐ ስለ ገባ ከእ ግዚአብሔር ሥርየትንና ፈውስን አግኝቶአል (፪ነገሥ፳-፩-፲፩ ኢሳ.፴፰-፩-፳፪)።

እንደዚሁም ንስሐ በአንድነት (በማኅበር) የሚፈጸም ታላቅ ምስጢር ነው። ከዚህም በላይ እን ደ ተገለጸው ንስሐ በብቸኝነት ብቻ ሳይሆን ሰዎች በአንድነት ሆነው ሲፈጽሙት ሥርየት ኃ ጢአትን የሚያሰጥ ሕግ ነው።

ለምሳሌ- ከመቶ ሃያ ሺህ በለይ የሚሆኑ የነነዌ ሰዎች በዮናስ ስብከት በአንድነት በጾምና በጸ ሎት ንስሐ ስለ ገቡ ከእግዚአብሔር ይቅርታንና ሥርየትን አግኝተዋል (ዩና ፫-፭-፲)።

## ቅዱስ ዩሐንስ መጥምቅ ሕዝብን ሲያስተምር «እንግዲህ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድር ጉ…»እያለ ይሰብክ እንደ ነበር የታወቀ ነው። (ማቴ ፫-፯-፱)

## <u>ጥያቄ፤</u> ለንስሐ የሚገባ ፍሬ ማድረግ ማለት ምን ማለት ነው?

ለንስሐ የሚገባ ፍሬ ማድረግ ማለት ከኃጢአት ሥራ ሁሉ በንስሐ ወደ መልካም ሥራ መመለ ስና መምህረ ንስሐ የሚሰጠውን የቀኖና ትእዛዝ መፈጸም ማለት ነው። የንስሐ ቀኖና ወይም ትእዛዝ ማለት መምህረ ንስሐ (የንስሐ አባት) የሚያዘውን ጾም፣ ጸሎት፣ ስግደት መፈጸም ፣ ምጽዋት መስጠትና የመሰለውንም መልካም ሥራ ሁሉ መሥራት ማለት ነው።

## <u>ጥያቄ </u>፣በንስሐ የተመለሱትን ምእመናን ስለሠሩት ኃጢአት እንዲጾሙ እንዲጸልዩ እንዲሰግዱና እንዲመጸውቱ ማዘዝ የሚችል ማነው?

የቅስና ሥልጣን ያለው ሰው ንስሐ መስጠት መናዘዝና ሥርየተ ኃጢአት (ይቅርታን) ማሰጠት ይችላል። የሌለው ግን ሥርየተ ኃጢአትን ለያሰጥ አይችልም። ይኸውም ጌታችን ኢየሱስ ክ ርስቶስ ለቅዱሳን ሐዋርያት በሰጣቸው ሥልጣን ተረጋግጦአል። ቅዱሳን ሐዋርያት የሰዎችን ኃ ጢአት በንስሐ ይቅር ይሉ ዘንድ የበደልንም ማስሪያ ይፈቱ ዘንድ ወይም ያስሩ ዘንድ ጌታችን እንዲህ ሲል ሥልጣነክህነት ሰጣቸው «እውነት እውነት እላችኋለው በምድር የምታስሩት ሁ ሉ በሰማይ የታስረ ይሆናል በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል» ማቴ. ፲፰- ፲፰)።

በሌላ ጊዜ ጌታችን «ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል የያዛችሁባቸውም ሁሉ ይያዝባቸዋል» ብሎ ለቅዱሳን ሐዋርያት ሥልጣን ክህነትን መስጠቱ ቅዱሳን ሐዋርያት ኃ ጢአት ይቅር የማለትና በደልንም በእግዚአብሔር ስም የመተው እንደዚሁም ሥርየትንና ይቅ ርታን የማስጠት ሙሉ ሥልጣነ ክህነት የተሾሙ ኤጴስ ቆጶሳትና ቀሳውስት ኃጢአተኞችን በ ንስሐ ኃጢአት ማሰሪያ የመፍታትና ይቅርታን ከእግዚአብሔር የማሰጠት ወይም ኃጢአተኞች ን በጌታ ቃል የማሰር ሙሉ ሥልጣን አላቸው።

**ጥያቄ፤ንስሐ ለሚገቡና ለሚናዘዙ ሰዎች የሚሰጠው ቀኖና ማለት ጾም፣ ስግደት፣ ምጽዋት በምን ይወሰናል?**

የሚሰጠው የቀኖና መጠን ብዛት ወይም ክብደት አንቀጸ ንስሐ በተባለው መጽሐፍ ተወስኖአል ወይም ተደንግጎአል። ሆኖም ለተነሳሕያኑን ከባድ ቀኖና መስጠት ተነሳሕያኑን ማስመረር ስለ ሚሆን ንስሐ አባቶች በዚህ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ይገናቸዋል። ስለዚሁ ጉዳይ የንስሐ አባቶ ች የጌታችን አርአያ መከተል ይገባቸዋል።ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለኑዛዜ ወደ እርሱ የመ ጡትን ኃጢአተኞችን፣ «ከዚህ የባሰ እንዳያገኝህ ደግመህ ኃጢአት አትሥራ። ከዚህ የባሰ እ ነዳያገኝሽ ደግመሽ ኃጢአት አትሥሪ» እያለ ይመልሳቸው ነበረ (ዩሐ ፭-፲፬ ፰-፲፩)

ስለዚህ የንስሐ አባቶች ካህናት በተነሳሕያኑ ለይ ከባድ ቀኖና እንዳይጫኑባቸው መጠንቀቅ ይ ገባቸዋል (ማቴ ፳፫-፬)። ይህም ማለት በተነሳሕያኑ አቅምና ጉልበት እየታየ መጠነኛ ቀኖና፤ (ጾም ስግደትና ምጽዋት) መስጠት (መሰጠት) አለበት ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁሉንም የሰ ው ልጆች በንስሐ ወደ እርሱ እንዲመለሱ የሚገፈልግ ርኅሩኅ አምላክ ነውና። ሁሉም ወደ ንስሐ እንዲደርሱ የሚፈልግ ርኅሩኅ አምላክ ነውና። ሁሉም ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል። ሲል ቅዱስጴጥሮስ ያስተማረው ስለዚህ ነው (፪ጴጥ.፫-፰-፲)

ሐዋርያው ቅዱስ ዻውሎስ ኃጢአተኞች በንስሐ እስኪመለሱ ድረስ እግዚአብሔር እንደሚታ ገሣቸውና ንስሐ የማይገባ እልከኛ ግን ለጥፋት እንደሚዘጋጅ እንዲህ ሲል አስረድቶአል፣ «አ ንተም እንደዚህ (ኃጢአት) በሚያደርጉ የምትፈርድ ያንንም የምታደርግ ሰው ሆይ አንተ ከእ ግዚአብሔር ፍርድ የምታመልጥ ይመስልሃል? ወይስ የእግዚአብሔር ቸርነት (ምሕረት) አንትን ወደ ንስሐ እንዲመራህ ሳታውቅ (የትዕግሥቱ ብዛት) ትንቃለህን? ነገር ግን እንደ አለመስማትህ ና ንስሐ እንዳለመግባትህየእግዚአብሔር ቅን ፍርድ በሚገለጥበት በቁጣው ቀን መቅሠፍትን (ፍ ዳን) በራስህ ላይ ታከማቻለህ» (ሮሜ ፪-፫-፭)

**ጥያቄ፤በንስሐ ወደ እግዚአብሔር የማይመለስ ኃጢአተኞ ሰዉ መጨረሻው ምንድን ነው?**

በንስሐ ወደ እግዚአብሔር የማይመለስ እልከኞ ሰው ፍጻሜው የሞት ሞት ነው። እግዚአብሔ ር በነቢዩ አንደበት እንዲህ ብሎአል «እነሆ ነፍሳት ሁሉ የእኔ ናቸው የአባት ነፍስ የእኔ እን ደሆነች ደግሞም የልጅ ነፍስ የእኔ ናት ኃጢአት የምትሠራ ነፍስ ግን እርስዋ ትሞታለች (ሕ ዝ፣ ፲፰-፬)።

**ጥያቄ፤-በንስሐ ውስጥ ያለ ሰዉ ማድረግ የሚገባው ምንድር ነው?**

በንስሐ ውስጥ ያለ ሰዉ ስለ ኃጢአቱና ስለ በደሉ ወደ  እግዚአብሔር መጸለይ መጾም መስገ ድና ማልቀስ ይገባዋል። እንዲህ ካደለገ ይቅርታንና ደኅንነትን ያገኞል። ስለዚሁም እግዚአብ ሔር እንዲህ ይላል ኃጢአተኞውም ከሠራው ኃጢአት ቢመለስ ፍርድንና ቅን ነገርንም መያ ደርግ ነፍሱን ይጠብቃታል። አስቦ ከሠራው በደል ሁሉ ተመልሶአልና ፈጽሞ በሕይወት ይኖ ራል እንጅ አይሞትም አይፈረድበትም።(ሕዝ፣ ፲፰፡፳፯-፳፱)

እያዘኑ እያለቀሱ ንስሐ መግባት እንደ ገና በጸጋ እንደመወለድ የሚቆጠር መሆኑን በርከት ያ ሉ አባቶች አረጋግጠዋል። ለምሳሌ ያህል ቅዱስ አትናቴዎስ «በሥጋ የተወለድን እኞንም ሦስ ት ልደት (ልደቶች) አሉን አንዲቱ ክርሰቶስን የምታስመስለን ቅድስት ጥምቀት ናት። ሁለተ ኞው በደልንና ኃጢአትን የሚያስተሰርይ የክርስቶስ ሥጋውና ደሙ ነው። ሦስተኞው ንጹሕ አድርጎ ወደ  እግዚአብሔር የሚያቀርበው በዮርዳኖስ አምሳል ከሰውነት ውስጥ የሚወጣው የ ንስሐ እንባ ነው»። ሲል አስረድቶአል (ጸሎተ ቅሳሴ ዘአትናቴዎስ ቁ ፶፪)።

ሶርያዊው ቅዱስ ማር ይስሐቅ «ቁርባናቲሆሙ ለጻድቃን አንብዐ አዕይንቲሆሙ» «የጻድቃን መባቸው የንስሐ እንባ (የዓይኖቻቸው እንባ) ነዉ። ብሎአል (ማር ይስሐቅ ገጽ፸)።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ደግሞ ፈጥነን ንስሐ መግባት የሚገባን መሆኑን እንዲህ እያለ ያስረ ዳል «ዘመናችን ሳይፈጸም እጁን ወደ እኞ ዘርግቶ የሚጠራንን እንስማው ፈጥን በፊቱ ራሳች ንን እናዋርድ። አቤቱ ጌታችን ሆይ እነሆ አንተን በደልን እኞን በዓይነ ምሕረት ተመልከት

ፍጥረቶችህን አትጣል ፍጥረቶች ነንና ከሞት በኃላ የሚያስብህ በመቃብር ተስፋ የሚያደርግ ህ መነው? እያልን ፈጥነን ንስሐ እንግባ» (ሃይማኖተ አበው ገጽ ፻፹-፲፩)። ቀጥሎም ይህ ቅዱስ አባት ሲመሰክር «እንኪያስ ፈጥነን ንስሐ እንግባ እርያዎች ከሚበሉት ተረንቃሞ (አሰር) መጥገብ አይቻልም ፈጣሪያችንን የሰማዩን የምድሩን ያህል አንተን በደልን ለንተ ልጅች መባል አይገባንምና ከአገልጋዩችህ እንደ አንዱ አድርገን እንጂ እንበለው» (ሉቃ ፲፭:፲፩-፳፬ ሃይማኖተ አበው ገጽ ፻፹፱:ቁ ፲፬)።

## ጥያቄ፤ስንት ጊዜ ንስሐ መግባት ይገባል?

ንስሐ ከሚደገሙ ምስጢራት አንዱ ስለሆነ ማለት ተደጋግመው ከሚፈጸሙት ምስጢራት አንዱ ንስሐ ነውና ኃጢአት በወደቁ ቁጥር ንስሐ መግባት ኃጢአት መናዘዝ ይገባል። በቅድሚያ አውቆ ንስሐ እገባለሁ ብሎ ኃጢአትን መሥራት ግን እግዚአብሔር መበደል ነውና አይገባም። ደጋግሞ ንስሐ መግባትና መናዘዝ እንደሚገና ቅድስ መጽሐፍ ሲያስረዳ «ጻድቅ ሰባት ጊዜ ይወድቃል ሰባት ጊዜም ይነሣል» ይላል (ምሳሌ. ፳፬፣፲፮)። ይኸውም ሳያውቅ በኃጢአት የሚወድቅ ሁሉ እንደ ገና በንስሐ መነሣት የሚችል መሆኑን ያረጋግጣል።

## ጥያቄ፤ንስሐ መግባት የሚያስፈልገው ምን ጊዜ ነው።

ንስሐ መግባት መናዘዝ የሚገባው ገና በሕይወተ ሥጋ ሳሉ አእምሮን ሳይደክም ነው። በኦርቶዳክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ትምህርት መሠረት ከሞት በኃላ ንስሐ የለምና እርጅና ሞት ሳይመጣ ንስሐ መግባትና የሠሩትን ኃጢአት መናዘዝ ይገባል (መክ.፲፪:፩-፰)

## ጥያቄ፤ንስሐን የሚሰጥና ኃጢአት የሚያናዝዝ ማን ነው።

ንስሐን መስጠትና ስለ ኃጢአትም ከእግዚአብሔር ይቅርታን ማሰጠት የሚችል በአንብሮተ እድ የተሾሙ ሥልጣነ ክህነት ያለው ሰው ነው።

ትምህርተ ሃይማኖት ኦርቶዶክሳዊት ከሚለው አቡነ ገብርኤል በ1991 ካዘጋጁት የተወሰደ።